www.abyssinialaw.com

16ኛ አመት ቁጥር 15 16th Year No 15	ባህር ዳር መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ.ም Bahir Dar 13th, October 2010

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት
ዝክረ-ሕግ
ZIKRE-HIG
OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 9.50 Price Birr	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	የ ፖ.ሣ.ቁ 312 P.o. Box

ማውጫ	Contents
ደንብ ቁጥር 81/2003 ዓ.ም	Regulation No.81/2010
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	The Amhara National Regional State Livestock Resources Development Promotion Agency Establishment, Council of Regional Government Regulation.

ደንብ ቁጥር 81/2003 ዓ.ም	REGULATION NO.81 /2010
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የእንስሳት ሃብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲን ለማቋቋም የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ	A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF LIVESTOCK RESOURCES DEVELOPMENT PROMOTION AGENCY IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE

www.abyssinialaw.com

በአማራ ብሔራዊ ክልል ውስጥ የተለያዩ ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ፈጣንና ቀጣይነት ባለው የኢኮኖሚ ዕድገት ውስጥ የእንስሳት ሀብትን በመጠበቅ፣ በመንከባከብና በማልማት ከፍተኛ ውጤት ማስገኘት እንዲቻል ለማድረግና የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ጥበቃ ሥራዎችን በባለቤትነት የሚመራ አካል ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has been found necessary to establish an institution which directs the development of livestock resource and health activities by its ownership, to ensure a higher output, in fast and sustainable economic growth, through implementing different policies and strategies of the region by protecting, preserving, and developing livestock resources;

በክልሉ ውስጥ የሚገኘውን የእንስሳት ሀብት በተሻለ ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል እንዲቻል ለዘርፉ ልማት ማነቆ የሆኑትን የዝርያ ምርታማነት አነስተኛ መሆን፤ የመኖ አቅርቦት ጥራት መጓደል፣ የበሽታ መስፋፋትና የገበያ እጥረት ለመግታትና ለመቅረፍ የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና አጠባበቁ ለእድገታችን ወሣኝ ሚና ያለው መሆኑ ስለታመነበት፤

WHEREAS, it is convinced that the development and health care of livestock resources has a crucial role in order to stop and solve the sectors development bottle-neck, problems as low productivity of breeds, low quality of food supply, spread of disease and market shortage, shortage, so as to enable a better use of livestock resource found in the region;

የክልሉን የእንስሳት ሀብት ልማትና ጥበቃው ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲጓዝ የሚደረገውን የልማት ጥረት ከማገዝ ጎን ለጎን በየጊዜው በዘርፉ የወጡና የሚወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ፕሮግራሞች ከገጠር ልማት ፖሊሲና ስትራቴጅ ጋር ማጣጣምና ውጤት ማስመዝገብ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it becomes necessary to score a result and to coincide the policy and strategy of rural development with policies, strategies, regulations, directives and programs issued in the sector, besides of the development effort being made to run the development and care of the regional livestock resources in a sustainable manner;

የእንስሳት፣ ውጤቶችንና ግብዓቶችን ንግድ ዝውውር ማስፈፀሚያ መመሪዎችን በመቅረፅ፣ በማሻሻልና በመተግበር ህጋዊ አሰራር እንዲሰፍን የሚያደርግና የሚከታተል ተቋም ማደራጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, it has been found appropriate to organize an institute which follow-up and cause to prevail a legal working system through planning, amending and implementing the execution directives of commercial transfer of livestock products and inputs;

www.abyssinialaw.com

ክልላችን በእንስሳት ሀብት በሀገርና በውጭ ንግድ ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ ለማድረግ ተከታታይ እንስሳት በሽታዎች ቅኝት ጥናት ቁጥጥር በማካሄድ ደረጃ በደረጃ ነፃ የበሽታ ቀጠና አካባቢዎችን ለመፍጠርና እንዲሁም የእንስሳት ኳራንቲን አገልግሎት መስጫ ጣቢያና የቁጥጥር ኬላዎችን በማቋቋም የበሽታ ቁጥጥር ስራዎችን ማጠናከር በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it is found necessary to strengthen the disease controlling work to make our regional livestock resources competent in local and foreign trade by performing a continuous survey of livestock diseases, step by step to create disease free zone areas by establishing animal quarantine service centers;

በክልሉ ውስጥ በእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና ጥበቃ ተግባር የተሰማሩ የግል ባሀብቶች፣ የልማት ድርጅቶችንና ሌሎች ተቋማትን በአግባቡ መደገፍ በማስፈለጉ ፤

WHEREAS, it is found necessary to support appropriately those private investors, development organizations and other institutions which are engaged in the activities of livestock resources and health development in the region;

የአማራ ብሔራዊ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ- መንግስት አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provision of Article 58 Sub Article 7 of the Revised National Regional Constitution, hereby issues this regulation.

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

PART ONE
GENERAL

1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የእንስሳት ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 81/2003 ዓ/ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

1. Short title

This regulating may be cited as "Livestock Resources Development Promotion Agency Establishment, Council of Regional Government Regulation No.81/2010"

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፦

1. "ቢሮ" ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ግብርና ቢሮ ነው፣

2. Definition

Unless the context requires otherwise, in this regulation:

1. "**Bureau**" shall mean the Amhara National Regional state Agriculture Bureau.

www.abyssinialaw.com

2. **"አርቢ"** ማለት አርሶ አደር ወይም አርብቶ አደር ሲሆን የግል ባለሀብቶችንና ሌሎች በእንስሳት እርባታ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን ወይም ድርጅቶችን ይጨምራል።

3. **"እንሰሳት"** ማለት የዳልጋ ከብት፣ በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ የጋማ ከብት፣ ዶሮ፣ ዓሣማ፣ ሰጎን፣ ጥንቸል፣ ንብ፣ የሐር ትልና የመሣሰሉትን ያጠቃልላል።

4. **"የእንሰሳት ምርትና ተዋፅኦ"** ማለት ወተትና የወተት ውጤቶች፣ ማር፣ ሥጋ፣ እንቁላል፣ ቆዳና ሌጦ፣ ፀጉር፣ ላባ፣ ቀንድ ፣ ሰም፣ ሸሆናና አጥንት፣ ሞራና የመሳሰሉትን የሚገልጽ ነው።

5. **"ጥራት"** ማለት የእንሰሳት ምርትና ተዋፅዖ ደረጃውን በጠበቀ አኳኋን ተመርቶ ለአገልግሎት የሚቀርብበት ሁኔታ ነው።

6. **"የገበያ ጥናት መረጃ"** ማለት የእንሰሳት ምርትና ተዋፅዖን ተፈላጊነትና የዋጋ ሁኔታ በመከታተል ማጥናትና መረጃዎችን መስጠት ወይም ማሰራጨት ነው።

7. **"የእንሰሳት በሽታ"** ማለት በእንሰሳው ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ የአካል እንቅስቃሴዎች ክንዋኔ ላይ የሚደርስ ያልተለመደ ችግር ነው።

8. **"ኳራንቲን"** ማለት እንሰሳትና የመኖ ዕጽዋት እንዲሁም የምርት ውጤቶቻቸውን ወደተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይገቡ ወይም ከተወሰኑ ሥፍራዎች እንዳይወጡ ለመቆጣጠር በማሰብ ማግለልና ከመሰሎቻቸው ለይቶ ማሣደግ ወይም ማስቀመጥና እንዳይሰራጩ ለማድረግ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክልል ውስጥ ማስቀመጥ ነው።

9. **"ከበሽታ ነፃ የሆነ ቀጠና"** ማለት አንድን የተመረጠ አካባቢ ተዛማችና ድንበር ዘለል የሆኑ የእንሰሳት በሽታዎችን በተከታታይ ቅኝትና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ከበሽታ ንክኪ ነፃ ተደርጐና ተከልሎ የተጠበቀ ቦታ ነው።

2. "**Animal Rearing**" shall mean a farmer or pastoralist including private investors and other people or organizations that are involved in animal husbandry.

3. "**Animal**" shall mean cattle, sheep, goat, camel, equine, poultry, pig, ostrich, rabbit, bee, silkworm and including others similar.

4. "**Animal products and by products**" shall mean milk and its by products, honey, meat, egg, skin and hide, wool, feather, horn, wax, hoof and bone, fat and the like.

5. "**Quality**" shall mean animal products and by products that are produced by keeping its standard quality to be available for specific purpose.

6. "**Market study data**" shall mean providing or distributing the demand and cost situation data of animal products and by products through follow up and studying it.

7. "**Animal disease**" shall mean the unusual problem occurred to affect the physiology of the external and/or internal body parts of the animal.

8. "**Quarantine**" shall mean a period during which animal, their feed and products, suspected of carrying a pathogen is detained at a port of entry or isolate and grow or preserve in restricted area under enforced isolation to prevent the spread of diseases from an area or region.

9. "**Disease free zone**" shall mean a clearly selected & regionalized area made free from a contagious or trans boundary animal diseases by putting in place a continual surveillance and control system there in.

www.abyssinialaw.com

ክፍል ሁለት
ስለ ኤጀንሲው መቋቋም፣ ተጠሪነትና ዓላማዎች

PART TWO
ESTABLISHMENT, ACCOUNTABILITY AND OBJECTIVES OF THE AGENCEY

3. መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የእንስሳት ሀብት ልማትማስፋፊያ ኤጀንሲ ከዚህ በኋላ "ኤጀንሲው" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግሥት መ/ቤት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል።
2. የኤጀንሲው ተጠሪነት ለክልሉ ግብርና ቢሮ ይሆናል።

3. Establishment and Accountability

1. The Amhara National Regional State Livestock Development Promotion Agency, hereinafter referred to as "The Agency", is hereby established as an autonomous government agency having its own legal entity under this regulation.
2. The Agency shall be accountable to the Regional Bureau of Agriculture.

4. ዓላማዎች

ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. የሃገሪቱን ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች መሠረት በማድረግ ተቋሙ ያስቀመጠውን ራዕይና ተልዕኮ ለማሣካት የሚያስችል ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለው የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣
2. በክልሉ ውስጥ የተለያዩ የስነ ምህዳርና የልማት ቀጠናወች ለሚገኙ አ/አደሮች፣ የግል ባለሀብቶች፣ ማህበራትና የመሳሰሉት ባላቸው የኢኮኖሚ አቅምና ስርዓተ ፆታን ባገናዘበ መልኩ አዋጭ አማራጭና ገበያ ተኮር ቴክኖሎጅዎችን በፍጥነትና በተሟላ ሁኔታ ለማቅረብ የሚያስችል የአሰራር ስልት መፍጠር፣
3. የዘርፉን መረጃዎች በተሟላ ሁኔትና በፍጥነት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ወቅታዊነቱን በጠበቀ ሁኔታ ለማድረስ የሚያስችል ስልት መቀየስ፣
4. የክልሉ የእንስሳትና የእንሰሳት ተዋፅኦዎች ጤንነታቸውና ጥራታቸው ተጠብቆ በሃገር

4. Objectives

The Agency shall, according to this regulation, have the following objectives:

1. To establish a responsible and accountable working system for the success of the vision and mission put by the Agency, in accordance with the national policies and strategies;
2. To create a system which enables to supply, in a fast and complete condition, a reliable option and market oriented technologies for the farmers, private investors, associations, and so on found in different agro ecological and development corridors of the region by taking into account their economic capacity and gender perspectives.
3. To create an information system that gives the beneficial community a complete, timely, fast and accessible data of the sector.
4. To accelerate the market system through keeping the quality and health of the

www.abyssinialaw.com

ውስጥና በአለም ገበያ ተቀባይነታቸውን ከፍተኛ ደረጃ ላይ በማድረስ የግብይት ስርዓቱን ማሳለጥ፤

regional livestock's and their products, and bringing their acceptance high both inside and in the world market.

5. ከአሁን በፊት በዘርፉ የነበሩትን የተበታተኑ የአደረጃጀትና የአሰራር ሂደቶች አስወግዶ በተቀናጀ ሁኔታ ሊናበብና ውጤት ሊያስመዝግብ በሚያስችል መልኩ ማደራጀት ፤

5. To remove the existing fragmented structural organization and function processes of the sector, and to reorganize same with well integrated and linked way so as to attain recordable results.

6. በተለምዶ ሲሠራባቸው የቆዩትን የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና አጠባበቅ ቴክኖሎጅዎችና የብዜት ማእከላት ውጤታማና ትርፋማ እንዲሆኑ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋትና ኢንተርፕራይዞችን በማቋቋም ዘለቄታዊ አገልግሎት እንዲሰፍን ወደ ግል ድርጅቶች የሚተላለፍበትን ብልሃት ማፈላለግ፤

6. To search for means to transfer the former traditional livestock resources development and health technologies, multiplication centres to private organizations, for the existence of a sustainable service, by forming enterprises and installing a system that enable them successful and profitable.

7. የእንሰሳት ሀብቱ የተፈጥሮ ሀብትና እንክብካቤውን በሚደግፍ ሁኔታ ጠቀሜታውን አጉልቶ ማውጣት።

7. To show magnificently the importance of animal resources in terms of supporting the natural resources.

5. መደበኛ አድራሻ

5. Principal Address

የኤጀንሲው መበደኛ አድራሻ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ይሆናል።

The principal address of the Agency shall be in the city of Bahir Dar.

ክፍል ሦስት

የኤጀንሲው ስልጣንና ድርጅታዊ አቋም

PART THREE

POWERS AND ORGANIZATIONAL STRUCTURE OF THE AGENCY

6. ስልጣንና ተግባር፦

ኤጀንሲው በዚህ ደንብ መሰረት ከዚህ በታች የተመለከቱት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ዘርፉን በሚመለከት ቀደም ሲል የወጡና ለወደፊት የሚወጡ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችን፣ አዋጆቸን፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በክልሉ ውስጥ ያስፈጽማል፣ ይቆጣጠራል፤

6. Powers and Duties

The Agency shall, pursuant to this regulation, have the following powers and duties:

1. Supervise and cause to be executed in the region those policies, strategies, proclamations, regulations, and directives issued before and to be issued in the future regard to the sector.

www.abyssinialaw.com

2. በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የእንሰሳት ዝርያዎች በልማት ቀጠናዎች ይለያል፣ የልማት ቀጠናውን መሠረት ያደረገ ስትራቴጅክ ዕቅድ ያዘጋጃ፣ ይተገብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
3. የእንስሳት መኖ ልማት ያካሄዳል፣ የግጦሽ መሬትና የእንስሳት ዝር እንዲሻሻልና እንዲጠበቅ ያደርጋል፤
4. የእንስሳት ሀብት ልማትና ጤና አጠባበቅ ፖኬጆችን ይፈጽማል፣ ይከታተላል፣ ከምርምር አካላት ጋር በመቀናጀት ያሻሽላል፣አዳዲሶችንም እየለየ ይቀርፃል፣ ቴክኖሎጂዎችን አባዝቶ ያስፋፋል፣
5. የእንስሳት ምርት ግብዓት አቅርቦትና ብድርን ያመቻቻል፣ያስተባብራል፤
6. የእንሰሳት የመጠጥ ውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር የውኃ እጥረቱ እንዲፈታ ያደረጋል፣ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
7. የሀገረሰብ እንስሳትን ለመጠበቅ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመሆን በቅንጅት ይሰራል፤
8. የእንስሳት ሃብት ልማቱን ከደን ልማቱ ጋር በማቀናጀት ከደን ልማት ውስጥ የሚገኙ ውጤቶችን በአግባቡ ለመጠቀም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርብ ይሰራል፤
9. አግባብ ካላቸው ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር ህጋዊና ህገወጥ የቁም እንሰሳት፣ የቆዳና ሌጦ፣የእንሰሳት እርድ፣ የግል እንስሳት መድሃኒትና የክሊኒክ አገልግሎት ንግድና ሌሎች ንግዶችን ይቆጣጠራል፣ የብቃት መስፈርቶችን ያወጣል፣ ማስረጃ ይሰጣል፣ በወጡና በሚወጡ ህጎች መሠረት እርምጃዎችን ይወስዳል፣ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

2. Identify the species of animals found in the region by development corridors; prepare a strategic plan based on development corridors; implement, follow -up and supervise same.
3. Undertake the development of livestock feed activities; cause to be safeguarded and improved the grazing land and livestock species.
4. Execute and follow – up the livestock resource development and health packages jointly with research bodies; identify, design, scale up and expand new technologies.
5. Co-ordinate and facilitate the supply of inputs and credit for animal production.
6. Facilitate conditions and cause to eliminate the problem of drinking water for livestock's where there is a shortage in area by discussing it with concerned bodies.
7. Work in harmony with concerned body to conserve local animals.
8. Work closely with concerned bodies, for the proper use of products found in the forestry, by integrating livestock resource development with forestry development.
9. Control the legal and illegal trade of livestock, skin and hide, livestock slaughter, private veterinary pharmacy and clinic service and other related trades with collaboration of proper stakeholders; formulate criteria and give legal document; take and cause to be taken measures based on the rules issued and to be issued in the future.

www.abyssinialaw.com

10. በክልሉ ውስጥ የእንስሳት ንግድ የጉዞ መስመሮችን በመለየት በሕግ እንዲታወቁና ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የኳራንቲንና የፍተሻ ማዕከላትን ያደራጃል፣ ከአጎራባች ክልሎችና ከፌዴራሉ መንግሥት አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፤

11. የበሽታ መከላከልን መሠረት ያደረገ የእንሰሳት ጤና አገልግሎት ይሰጣል፣ የእንሰሳት በሽታዎች ምርመራ፣ አሰሳና ቁጥጥር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የእንሰሳት እንቅስቃሴን ይገድባል፣ ክልል አቀፍ የበሽታ ቁጥጥር ስትራቴጂ ይነድፋል፣ ነፃ የበሽታ ቀጣናዎችን ያቋቁማል፤

12. ለዘርፉ ልማትና ጥበቃ የሚያስፈልጉ መሰረተ ልማቶችን ያቋቁማል፣ እንዲቋቋሙና እንዲስፋፉ ያደርጋል፣ አደረጃጀታቸውን በማሟላት ሙሉ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፤

13. ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ከበሽታ ነፃ የሆነና ጥራቱ የተጠበቀ ስጋ እንዲቀርብ በቄራዎች የሥጋ ምርመራ እንዲካሄድ ያደርጋል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ደረጃቸውን የጠበቁ ቄራዎች በየከተሞች እንዲገነቡ ያደርጋል፤

14. በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ጥራትና ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳት ምርት እንዲያቀርቡና አገልግሎት እንዲሰጡ ያደርጋል፣ የአቅም ግንባታ ሥራና የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

15. ለእንስሳት ምርቱ የገበያ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የገበያ መረጃ ለተጠቃሚው በወቅቱ እንዲደርስ ያደርጋል፤

16. በየደረጃው የእንስሳት ጤና አጠባበቅ አገልግሎትን ለማሻሻል የሚያግዙ የእንስሳት እርባታና ጤና ባለሙያዎች ምክር ቤቶችን

10. Cause to be legally recognized and protected properly of those animal trade trekking routes, in the region, by identifying them; organize quarantine and checking centres; work in collaboration with neighbouring regions and bodies of the federal government.

11. Render health service of livestock's based on prevention of disease; undertake diagnosis, observation and controlling activities of animal diseases; restrict , if it is found necessary, livestock's movement; design regional disease controlling strategy and establish disease free corridors.

12. Establish and cause to be established and expanded the infra/super structures that are necessary for the development and protection of the sector, and cause them to give full service by fulfilling their organization.

13. Cause to be made a meat inspection by abattoirs in order to provide disease free and qualified meat for the consumers; cause to be constructed standard abattoirs in cities by cooperating with concerned bodies.

14. Encourage investors engaged in the sector, to supply and serve qualified and standardized livestock products; provide them capacity building and professional support.

15. Facilitate market conditions for the livestock products; cause to be provided a market data for the beneficiary on time.

16. Establish, follow – up and support the council of animal husbandry and health professionals, which help to improve

www.abyssinialaw.com

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ያቋቁማል፣ ይከታተላል፣ ይደግፋል፤

animal health services at various levels, in collaboration with concerned bodies.

17. ውሎችን ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በህግ መሠረት ይከሣል፣ ይከሰሳል።

17. Enter in to contracts, own property, sue and be sued based on law.

7. ድርጅታዊ አቋም

ኤጀንሲው በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ ሲሆን ለሥራው የሚያስፈልጉ የበታች የሥራ ሀላፊዎችና ደጋፊ ሠራተኞች ይኖሩታል።

7.Organizational Structure

The Agency shall be led by a Director General; provided, however, that it shall have subordinate heads and support employees necessary for the work.

8. ስለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አሿሿምና ተጠሪነት

1. የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለቢሮው ይሆናል።

2. ዳይሬክተሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ድንጋጌዎች ሥር ለኤጀንሲው የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል።

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዳይሬክተሩ ከዚህ በታች የተመለከቱት ልዩ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ የኤጀንሲውን ስራዎች በበላይነት ይመራል ያስተዳድራል ይቆጣጠራል፤

ለ/የኤጀንሲውን የአጭር፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ዕቅድ ይነድፋል፣ ያስፈፅማል፤

ሐ/ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ህግ መሠረት የኤጀንሲውን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

መ/ ለኤጀንሲው በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ኤጀንሲውን ይወክላል፤

8. Appointment and Accountability of the Director General of the Agency.

1. The Director General of the Agency shall, having been appointed by the Head of the Regional state, be accountable to the Bureau.

2. The Director General shall implement the powers and duties vested for the Agency under the provision of Article 6 of this regulation.

3. Without prejudice to the general provision of sub article 2 of this Article hereof, the Director General shall have the following specific powers and duties;

a/ Lead, administer and control the works of the Agency.

b/ Draft short, medium and long-term plan and cause to be executed.

c/ Employ, administer and dismiss the staff of the Agency pursuant to the law of the Regional Civil Service.

d/ Effect financial expenditures in accordance with the program and budget approved for the Agency.

e/ Represent the Agency whenever there are dealings to be carried out with third parties.

www.abyssinialaw.com

ረ/ ለስራው ባስፈለገው መጠን ከስልጣንና ተግባሩ ውስጥ ከፊሉን ለኤጀንሲው የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

f/ Delegate part of his powers and duties, as necessary for work, for the subordinate heads and staff of the Agency.

9. ስለ ምክትል ዳይሬክተር

1. ኤጀንሲው እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የሚሾም ምክትል ዳይሬክተር ይኖረዋል።
2. ምክትል ዳይሬክተሩ ተጠሪነቱ ለዳይሬክተሩ ሆኖ፤
   - ሀ/ በዳይሬክተሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፤
   - ለ/ ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሰራል።

9. Deputy Director

1. The Agency may, as its necessity, have the Deputy Director appointed by the Head of the Regional Government.
2. The Deputy Director shall be accountable to the Director General and hence:
   - a. Carryout the specified tasks given by the Director.
   - b. Represent the Director and carry out his official functions where he is absent or unable to perform his duty.

ክፍል አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

PART FOUR
MISCELLANEOUS PROVISIONS

10. ስለበጀት

የኤጀንሲው በጀት በክልሉ መንግሥት ይመደባል።

10. Budget

The budget of the Agency shall be allocated by the Regional Government.

11. ስለ ሂሣብ መዛግብት

1. ኤጀንሲው የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብትን ይይዛል
2. የኤጀንሲው የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሰነዶች በክልሉ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየጊዜው ይመረመራሉ።

11. Books of Account

1. The Agency shall keep complete and accurate books of account.
2. The books of account and financial as well as property related documents of the Agency shall be audited timely by the Office of Auditor General of the Regional State or by the auditors to be designated by it.

www.abyssinialaw.com

12. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ ደንብ ውስጥ በተሸፈኑት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

13. መብትና ግዴታ ስለማስተላላፍ

ኤጀንሲውን የሚመለከቱት ሆነው በቀደምት ህግጋትና ደንቦች አማካኝነት ለቢሮው ተሠጥተው የነበሩ መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ መሠረት ወደተቋቋመው ኤጀንሲ ተላልፈዋል።

14. መመሪያ የማውጣት ስልጣን

ይህንን ደንብ በተሟላ ሁኔታ በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን መመሪዎች ኤጀንሲው ሊያወጣ ይችላል።

15. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
መስከረም 26 ቀን 2003 ዓ/ም
አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

12. Repealed and Inapplicable Laws

Any other regulation, directive, or customary practices which are inconsistent with the issues covered under this regulation shall not be applicable thereto.

13. Transfer of Rights and Obligations.

The laws and regulations reflecting the rights and obligations of the Agency, that were vested for the Bureau, are hereby transferred to the Agency established as per this regulation hereof.

14. Power to Issue Directives

The Agency may issue directives necessary for the full implementation of this regulation.

15. Effective Date

This Regulation shall come in to force as of the date of its publication on the Zikre – Hig Gazette of the Regional State.

Done at Bahir Dar
This 6th day of October, 2010
Ayalew Gobezie
Head of the Government of the
Amhara National Regional State